# የወረስኩት ቆራጥ ወኔ

ከመዝገቡ አሰፋ

ክንዶቼም አሉ ጠና ጠና

ልጓዝ በአርበኞች ትግል ፋና

በወደቁት ሰማእታት ቃል ልፀና።

ልዘጋጅ ለፋኖው ለደፈጣው

የጠላትን ምሽግ ላውላልቀው ።

አይፈታኝም የወያኔ ሽብር

አይገታኝም ለፍትህ ለእኩልነት ከመጋተር።

ላልበገር ለአድርባዩ ሽርብ ገመድ

ፍንከች ላልል ለአሜከላ ለእንክርዳድ።

አለኝ የወረስኩት ቆራጥ ወኔ

ከፀጋዬ ከሳሙኤል ከብርሃኔ።

እሄዳለሁ ተራራውን ወጥቼ

እጉዛለሁ ሜዳውን አቋርጬ።

እገባልሁ ከደኑ ጥቅጥቅ ካለው

ጡሩን በጦር ልመልሰው።

እየዘመርኩ የትግሉ ነው ህይወቴን

ፍፁም ነው እምነቴን።

ብረት አነሳሁ

ለትግል ተነሳሁ።

ጠላት ይፈራ ይሸበር

የአድርባይ ቅስሙ ይሰበር።

ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ

ለሕዝባዊ ሥርዓት ልምላሜ።

ፍፁም ነው እምነቴ

የትግሉ ነው ህይወቴ።

(ግንቦት 2007 ዓ.ም )